## 8. ብዙ ብሄሮችና ባህሎች ባሉበት ህብረተሰብ ሰላምና ልማት ስለሚገኙባቸው ሁኔታዎች፣

### 8.1 የአልጀሪያ ምሳሌ፣

በአቶ መሃመድ ካገድሪሽ
አልጀርስ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር

በአልጀሪያ ህዝቡ በተለያዩ ማህበራት በመስኩ በነጻ ተደራጅቶ መንቀሳቀስ የጀመረው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው:: የህዝቡ በማህበራት መደራጀት በሶሻልና በባህላዊ፣ በፖለቲካና በኢኮኖሚው ኑሮው ሊያመጣ የሚችለውን አስተዋጽኦ በመገንዘብ አዲሱ የ1989 ዓ.ም. ህገ መንግሥት ይህንን የመደራጀት መብት አጸደቀ:: በእርግጥ ቀደም ሲል ህዝቡ የመደራጀት መብት ነበረው:: ነገር ግን ይህ መብት በስፖርት፣ በባህልና በአንዳንድ የተወሰኑ ሶሻል ዘርፎች ብቻ የታወቀ ነበር:: ለዚያውም የባለሥልጣኖች ጥብቅ ቁጥጥር ነበር::

ነገር ግን ደግሞ ምንም እንኳን ዛሬ በምናየው መልክ የተደራጁ ማህበራት ቀደም ሲል ባይኖሩም ህዝቡ ከድሮም ጀምሮ በማህበራዊ ኑሮው በመረዳዳትም ሆነ አንዳንድ የጋራ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት የሚያስችሉት ማህበራት የማቋቋም ልምድ ነበረው:: በዚህ ልምድ መሠረት ለመረዳዳትም ሆነ በጋራ ለመሥራት በማህበር የሚቋቋሙ አባላት በባህል የጸደቁ ግዴታዎች ነበሩአቸው: ይህንን ግዴታ የማያከብሩ ወይም የጣሱ ግለሰቦች ለማህበሩ የሚከፍሉት ካሣ ዓይነት ነገር ነበር:: ይህ ካሣ ለማህበሩ በነጻ ሥራ የማበርከት ወይም አባላት የተስማሙበት ሌላ ነገር ሊሆን ይችላል:: ይኸንን አሻፈረኝ የሚል ግለሰብ መቀጮ ይበየንበታል:: ይህ መቀጮ በገንዘብ ሊሆን ይችላል ከሁሉ የሚፈራው መቀጮ ግን ከመንደሩ ማህበረሰብ መገለል ነበር::

አልጀሪያ ነጻ ከወጣች በኋላ መንግሥት እንዲህ ዓይነቱን የአደረጃጀት ልምድ ሆን ብሎ አዳከመው:: ህዝቡ በራሱ አነሳሽነት እየተደራጀ ችግሮቹን በማህበር መወጣት ልምዱ እየቀረ ሥራው ሁሉ የህብረተሰቡን ችግሮች ሁሉ እኛ እንፈታለን በሚሉ የመንግሥት ተቋማት ተያዘ:: በዚህ መልክ ፖርቲም መንግሥትም የሆነው ሃይል በህብረተሰቡ ህይወት ላይ ሞኖፖሉን ተከለ:: ተደራጅተው መንቀሳቀስ የሚችሉት የፖርቲውና የመንግሥቱ አካል የሆኑት "ህዝባዊ ማህበራት" ብቻ ነበሩ::

በ1990 ዓ.ም. በታህሣሥ ወር የወጣው አዋጁ ማህበር በነጻ እንዳይቋቋም ያግዱ የነበሩትን ማነቆዎች ሁሉ አስወገዳቸው:: በመንደሩና በየቀበሌው ታፍኖ የነበረው ህዝብ ለመደራጀት ተነሳሳ:: ይህ የመደራጀት ንቅናቄ እየሰፋ ሲሄድ በዚህ መልክ የሚቋቋሙ ማህበራት ከመንግሥት ጋር መደራደር የሚችሉ ኃይሎች እየሆኑ መጡ:: እስከአሁን ድረስ የመንግሥት ሥራዎች ተብለው ከተከለሉ ተግባሮች ውስጥ አንዳንዶቹ ወደ እነዚህ ማህበራት መዛወር ጀመረ:: ለዚህም ማህበራትና መንግሥት እየተደራደሩ ሥራ እስከ መከፋፈል ደረሱ::

በነጻና በገዛ ፈቃድ የመደራጀት መብት በመረጋገጡ ዓላማ አለን፣ ይኸን ፕሮዥ ከሥራ ላይ እናውላለን የሚሉ ታታሪ ግለሰቦች ሁሉ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ማህበራዊ አደረጃጀት ልማድ መልሰው ነፍስ ይዘሩበትና ይደራጁ ጀመር:: ቀደም ሲል መንግሥት ያዳከማቸው የነበሩት ማህበራት አሁን በህግ የታወቁ ማህበራት ሆኑ:: ለአጭር ጊዜና እለት ተእለት ችግሮችን ለመፍታት ብቻ ሳይሆን በረዥም ጊዜና በልማት ዓላማዎች ዙሪያ የተደራጁ ማህበራት በያለበት ፈለቁ:: በጥቂት ወራት ውስጥ ከ30,000 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ ማህበራት ተመዘገበው

### 3. የቼኮስሎቫኪያ ምሳሌ፣

በአቶ ክሪስቶፍ ሳንገ/ወንጌላዊ አገልግሎት ፕራግ ቼኮዝሎቫኪያ/ ገለጻ

በኛ ሀገር ያለው ችግር በቼኮችና በስሎቫኪያ መሃከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ነው:: ብዙ ሰዎች የሁለቱንም ህዝቦች መብት የሚያረጋግጥ የፌዴራል መንግሥትን ሥልጣን በግልጽ የሚወስን አዲስ ህገ መንግሥት እንዲወጣ ይጠይቃሉ:: የሀገሪቱ መሪዎች ወደ ካናዳ ፣ ስፔን ...እየሄዱ በነዚህ አገሮች የተገኙትን መፍትሄዎች በማጥናት ላይ ናቸው::

ችግሩ አዲስ አይደለም:: ግን በኮሚኒስቶች አገዛዝ ሥር በነበርንበት ዘመን ጥያቄው አይነሳም ነበር:: አሁን ይፋ ወጥቷል:: የገበያ ኢኮኖሚ ሲመጣ የተለያዩ ጥቅሞች ይጋጫሉ:: ለምሳሌ ቼኮች የአውሮጳ የጋራ ገበያ አባል መሆን ይፈልጋሉ:: ከጠቅላላው ህዝብ 1/3 የሆኑት ስሎቫኮች ደግሞ ይሄንን አይፈልጉም::

በሽግግሩ ዘመን የፈለቀ ብዙ የኢኮኖሚ ችግሮች አሉ በተለይ በስሎቫኪያ የሥራ አጥነት ችግር እየተባባሰ መጥቷል:: በሚመጡት ወራት ብዙ የፖለቲካ ችግሮች መፈጠራቸው የማይቀር ነው:: ይህ የፖለቲካ ችግር ደግሞ ወደ ግጭቶች የሚያመራ ነው::

በዚህ ክፍለ ዘመን ቼኮስሎቫኪያ ደጋግማ በውጭ ኃይሎች ተወራለች:: ሁሉም ብሄሮች በነዚህ ወራሪዎች ሳቢያ ስቃይ ደርሶባቸዋል:: 1938 ዓ.ም. ስሎቫኮች በሪፐብሊኩ መንግሥት ተበደልን የሚል ስሜት ስለነበራቸው በናዚዎች ወረራ በመጠቀም የራሳቸው መንግሥት አቋቁመው ነበር:: ከዚያ በኋላ ከ1938 እስከ 1945 ዓ.ም. ድረስ ስሎቫኪያ ከቀሪት የቼኮስሎቫኪያ ግዛቶች የፈጠነ የኢኮኖሚ እርምጃ አድርጋ ነበር:: ዛሬ ይሄንን ሁኔታ በማስታወስ ፋሽስታዊው ቡድኖች በስሎቫኪያ እያደጉ ሲሄዱ እናያለን::

የሀገሪቱን አንድነት ለመጠበቅ ታሪክን ደጋግሞ ማንሳት አይበቃም:: በተለይ ደግሞ የኮሚኒስቶች አገዛዝ ይህንን የታሪክ ቅርስ ደጋግሞ ሊጠቀምበት ይሞክር ስለነበር ዛሬ እሱን ማንሳት አያዋጣም::

በሃገራችን ሽማግሌዎች የሆኑት አሁንም በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ተቋቁሞ የነበረውን የመጀመሪያውን ሪፐብሊክ ያስታውሳሉ:: ግን ደግሞ በጀርመን ወረራ ጊዜ አልደረሱልንም በማለት በምእራቦች ላይ ቅሬታ አላቸው እንዲያውም በዚህ የተነሳ ናዚ ጀርመኒን በደንብ ስለተዋጉ ኮሚኒስቶች ዝነኛ ሁነው የሚታዩበት ሁኔታ አለ::

የሚቀጥለው ትውልድ ደግሞ የዲሞክራሲ ልምድ የለውም:: እርግጥ ነው "የፕራግ ጸደይ" የተባለውን የሪፎርም ዘመን ያየ ትውልድ ነው:: በዚያን ጊዜ በኮሚኒዝምና በካፒታሊዝም መሃከል "ሶስተኛ ጎዳና" ሊኖር ይችላል የሚል እምነት የነበረው ትውልድ ነው:: ግን ይሄ "ሶስተኛ ጎዳና" አልተገኘም:: በአመጽና በጭቆና የህዝቡን ህልም በመስበሩ ኮሚኒስት ፓርቲው የነበረው ተቀባይነት አሽቆለቆለ ይህ ህልም መሰበሩ በቼኮስሎቫኪያ ህብረተሰብ ያስከተለው መዘዝ እስከ ዛሬ ሁላችንንም ይሰማናል::

የመጨረሻው ትውልድ በ1970—1980 ዓመታት መሃከል ያደገው ትውልድ ነው:: በዚህ ዘመን አንዳንድ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ለህዝቡ በማደረስ ኮሚኒስት ፓርቲው ሃገሪቱን ለማረጋጋት ሞከረ:: በዚህ ሰቢያ ህዝቡ ቀስ በቀስ የምእራባውያንን ልምድ እየያዘ ሄደ:: እምነታቸውን እያጡ የሄዱትን ኮሚኒስቶች ሥልጣን ለመገርሰስ የበቃው ይኸ ትውልድ ነው::

በ1989 ዓ.ም. የተካሄደው አብዮት "ከሄራዊ አብዮት" ሳይሆን በቀረው በአውሮጳ ከሚከሄደው ለውጥ ጋር አብሮ ለመራመድ ሲባል የተደረገ ለውጥ ነው:: በዚህ ሄደት ውስጥ የምእራቦችን ዲሞክራሲና የኑሮ ዘዴ በጣም አድርጉ የሚያነቅና የማምለክ ሁኔታ ተፈጥሮአል:: እንግዲህ ዛሬ ሁሉም የሚጠይቀው መጪው ጊዜ የሚፈለጋቸውንና እያደጉ የሚሄዱትን ችግሮችና ቀውሶች ህብረተሰቡ እንዴት ሊቋቋማቸው ይችል ይሆን የሚለውን ጥያቄ ነው::

ዝምብሉ በደፈናው ዲሞክራሲ ማለት አይበቃም:: በአንድ የሽግግር ዘመን ዋናው የሚፈለገው ህብረተሰቡ የሚተልማቸውን ዓላማዎች በቁጠባ ከግብ ማድረስ ነው:: በ1989 የቼኮስሎቫኪያ ህዝብ ፖለቲካ በቃኝ የሚል ህዝብ ነበር:: በዚያን ጊዜ እንደ ዋና ዓላማና ምኞት አድርጉ የያዘው የሰው ልጅ መብት የሚለውን ጥያቄ ነበር:: ዛሬ ግን ይኸ እንደ ዋና ነጥብ ተደርጉ አይወሰድም:: ዛሬ ዋናው መለኪያ መንግሥት ለህዝቡ ቁጠባዊ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች የሚሰጠው መፍትሄ ነው:: ከዚህ ችግር አንጻር ሌሎች ሁሉ ማለትም የተፈጥሮ አከባቢ፣ ሰላም ባህል፣ የሰው ልጅ መብት የድር ክብደታቸውን እያጡ ነው::

በዚህ ሁኔታ በተለያየ የእድገት ደረጃ የሚገኙ አካባቢዎች በምን ዘዴ ችግራቸውን በጋራ እየፈቱ በአንድነት ሊኖሩ ይችላሉ የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም:: ከዚህ አንጻር አብዛኛው ሰው ከአውሮጳ ከገበያ ኢኮኖሚ ብዙ ይጠብቃል::